# በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የንግድ ሚኒስቴር

# የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት አፈጻጸም

# መመሪያ

የካቲት 30/2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት

መመሪያ ቁጥር 869/2014

# የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓት መመሪያ

የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓትን ለማስፈጸም በወጣው አዋጅ ቁጥር 819/2006 በአንቀጽ 18 ንኡስ አንቀጽ 2 ለንግድ ሚኒስቴር በተሰጠው ስልጣን መሰረት የአዋጁንና ደንቡን አሰራር ለማስፈጸም ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅንና እሱን ተከትሎ የወጣውን ደንብ ቁጥር 341/2007 ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 869/2014 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፣

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ ‹‹ ደንብ ›› ማለት የቁም እንስሳት ግብይት ደንብ ቁጥር 341/2007 ነው፣

2/ ‹የአገልግሎት ክፍያ›› ማለት የግብይት ተዋንያኑ በግብይት ላገኙው አገልግሎት የሚፈፅመው ሕጋዊ ክፍያ ነው።

3/ በቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 819 /2006 አንቀፅ 2 እና እሱን ተከትሎ በወጣው ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀፅ 2 የተመለከተው ትርጓሜ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

## ክፍል ሁለት

## ስለ የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ግብይት፤ አከላለል፤ አደረጃጀት እና አስተዳደር፤

### 3. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት

1. ወደ መጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት እንስሳትን ለመግዛት የሚመጣ ማንኛውም ፤

ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

Ministry of Trade Archives

ሀ) ግለሰብ ሽማቾች የቁም እንስሳትን ለዕለት ፍጆታ፣ ለሰርግ፣ ለልደት እና ለመሳሰሉት የሚገዙትን ቁጥር የፍጆታቸውን መጠን መግዛት ይችላሉ፡ ሆኖም አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ የግብይት ተቆጣጣሪዎች ሊያጣሩ ይችላሉ።

ለ) የድርጅት ሸማች የቁም እንስሳትን ለሆቴል፣ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ቀለብ፣ ለማረሚያ ቤቶችና ለፖሊስ ተቋማት፣ ለመከላከያ ሰራዊት ቀለብ እና ለመሳሰሉት ተግባራት የሚገዙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ መግዛት አለባቸው።

ሐ) የቁም እንስሳትን ለእርባታ፣ ለምርምር እና ለመሳሰሉት ተግባራት ለማዋል መግዛት የሚፈልጉ ድርጅቶች ማስረጃቸውን በማቅረብ የፍላጎታቸውን መጠን የሚጠቅስ ከአካባቢው አስተዳደር የድጋፍ ደብዳቤ በማምጣት መግዛት አለባቸው።

መ) ህብረት ስራ ማህበራት ህጋዊነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃዎች ለግብይት ተቆጣጣሪው ማሳየት አለባቸው።

2. ከላይ በተራ ቁጥር 3.1 ንኡስ ፊደል ለ እና ሐ የተገለጹት የግብይት ተዋንያኖች ለተፈለገው አላማ ስለማዋላቸው የግብይት ተቆጣጣሪዎች ሊያጣሩ ይችላሉ።

3. ያልተሸጡ ከሆነ ምንም ዓይነት የአገልግሎት ክፍያ ሳይጠየቅባቸው ወደ መጡበት ይመለሳሉ።

## 4. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት አከላለልና አደረጃጀት

1. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ሲደራጁ ለአርቢው በቅርብ ርቀት ቢበዛ እስከ 12 ኪሎ ሜትር ቢሆን ይመረጣል። እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ የግብይት ማዕከላት ሊቋቋሙ ይችላሉ።
2. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ብዛትና ስርጭት ሲወስን ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤና፣ ከዕምነትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ቢያንስ 500 ሜትር ርቀት ላይ መገኘታቸውን፡ እና ሌሎችም ለግብይት ስርዓቱ አመቺነት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ከግምት መግባት ይኖርባቸዋል፣
3. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት አከላለል ግብይቱን ለማስተናገድ ያለው መስፈርቶችን አሟልቶ መገኘት እንጂ የአካባቢ አስተዳደር ወሰንን መሠረት ያደረገ መሆን የለበትም።
4. በደንቡ ቁጥር አንቀጽ 5 መሰረት የሚቋቋም የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት

ሀ/ የውሃ ማጠጫ ገንዳና ማጠራቀሚያ ታንከር እንዲሁም የውሃ አገልግሎት፣

ለ/ የደረቅ መኖ መመገቢያ ገንዳ፣

ሐ/ የመጠለያ ታዛ፣

መ/ የጭነት መኪና ማስገባትና ማስወጣት የሚችሉ በሮች፣



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

ሠ/ እንደአካባቢው የእንስሳት አቅርቦት አይነት የሚወሰን ሆኖ ለዳልጋ ከብት፣ ለበግና ፍየል፣ ለጋማ ከብት ለየብቻ የተከፋፈለ የመገበያያ ቦታ ያለው መሆን አለበት፣

ረ/ በተፈጥሮ አካባቢው ወይም ማህበረሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን የደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ እና ፈሳሽ ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሰራር /Drainage system/ ያለው መሆኑ

ሰ/ የእንስሳት መለያ ለመስጠት የሚያስችሉ አስፈላጊ ቁሳቁሶች( የጆሮ መለያ ቁጥር፣ የጆሮ መለያ ማያያዣ፣ የክትባት ግርግም) ያለው መሆኑ

ሸ/ የጥበቃ ማማ፣

ሊኖሩት ይገባል፤

## 5. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት አስተዳደር

1. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላትን የሚያስተዳድረው የቀበሌ አስተዳዳር ወይም የማዘጋጃ ሹም የሚመራው የግብይት ማዕከሉ በሚገኝበት ቀበሌ ወይም ከተማ አስተዳደር የሚገኙ የግብርና ባለሙያዎች፣ የቀበሌ ስራ አስኪያጅ፣ የጸጥታ አካል እና ሌሎችንም የሚያካትት የተዋቀረ ኮሚቴ ያስተዳድራቸዋል፤
2. በመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ግብይት ተግባራዊነት በአካባቢው በሚገኝ ቀበሌ ወይም ከተማ አስተዳደር የሚደራጅና የሚተዳደር ይሆናል፤
3. የመጀመሪያ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላትን የሚያስተዳድረው አካል በቁም እንስሳት ገበያዎች ውስጥ መሠረተ-ልማቶችን እንዲሟሉ ያደርጋል፤
4. የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ተደራሽ ለማድረግ የቁም እንስሳት የገበያ ቦታዎችን ያደራጃል፤
5. የቁም እንስሳት ግብይቱ ግልፅ፣ ፍትሃዊና ተጠያቂነት የሰፈነበት የግብይት ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፤
6. የቁም እንስሳት ገበያዎች በተፈቀደላቸው የሰው ኃይል እንዲደራጁ በማድረግ፣ ሰራተኞቹ በአግባቡ ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን መከታተል፣ እንዲሁም በአሠራር ላይ የግንዛቤ ክፍተትን በመለየት ለባለሙያዎች ስልጠና እናዲያገኙ ያደርጋል፤
7. የግብይት ተቆጣጣሪው፣ ከፀጥታ ሀይል እና ሌሎችም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ገበያው በሥርዓት እንዲመራ ያደርጋል፣

## 6. የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት

1. ወደ ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት የሚቀርቡ የቁም እንስሳት የደለቡ/የሞከቱ ወይም ለእርድ የተዘጋጁ ብቻ ስለሚሆኑ በጊዜው ካልተሸጡ በገበያ ማዕከሉ ማቆያ ቦታዎች እስኪሸጡ ይቆያሉ።



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

2. ግለሰብ ሸማች የቁም እንስሳትን ለዕለት ፍጆታ፣ ለሰርግ፣ ለልደት እና ለመሳሰሉት የሚ ቁጥር የፍጆታቸውን መጠን መግዛት ይችላሉ፡ ሆኖም አጠራጣሪ ሆኖ ሲገኝ የ ተቆጣጣሪዎች ሊያጣሩ ይችላሉ፡፡

3. የድርጅት ሸማች የቁም እንስሳትን ለሆቴል፣ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች፣ ለማረሚያ ለፖሊስ ተቋማት፣ ለመከላከያ ሰራዊት ቀለብ እና ለመሳሰሉት ተግባራት የሚገዙ መንግ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ማንነታቸውን የሚገልጽ ማስረጃ በማቅረብ መግዛት አለባቸ

4. የቁም እንስሳትን ለምርምር እና ለመሳሰሉት ተግባራት ለማዋል መግዛት የሚፈልጉ ድ ማስረጃቸውን በማቅረብ የፍላጎታቸውን መጠን የሚጠቅስ ከአካባቢው አስተዳደር የ ደብዳቤ በማምጣት መግዛት አለባቸው፡፡

5. ከላይ በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተገለጹት የግብይት ተዋንያኖች ለተፈለገው አላማ ስለማዋ የግብይት ተቆጣጣሪዎች ሊያጣሩ ይችላሉ፡፡

6. ቁጥራቸው ከ20 በላይ የሆኑ የቁም እንስሳትን የሚያቀርቡ አርቢዎች፣ አድላቢዎች፣ ህ ስራ ማህበራት ሁሉንም የቁም እንስሳት ወደዚህ የግብይት ማዕከላት ማ ሳያስፈልጋቸው በሚያቀርቡት የቁም እንስሳቱ ናሙና ወይም ኤሌክትሮኒክስ መግለጫ መ ግብይት መፈፀም ይችላሉ፡፡

7. በጨረታ ለሚፈጸም ግዢ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 6 መሰረት የቁም እንስሳት አይነት በማድለቢያው ወይም በማቆያ ጣቢያው ስለመኖራቸው በአካባቢውያቸው ከ አግባብነት ካለው አካል ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡

8. በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት በኤሌክትሮኒክስ መግለጫ መሰረት በወካይ ናሙና መሰረት የሚፈፀም ግብይት በፅሁፍ ውል መፈፀም አለባቸው፡፡

9. ግብይቱ በግብይት ተቆጣጣሪው ከተረጋገጠ በኋላ የማጓጓዣ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት እንስሳቱ ርክክብ በሚገኙበት ቦታ በማድለቢያ ወይም በማቆያ ጣቢያው ይደረጋል፡፡ መልስ ለግብይት ተቆጣጣሪው ይልካል፡፡

## 7. <u>የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት አከላለልና አደረጃጀት፤</u>

1. ነባር የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን በመለየት በህብረተሰቡ ዘንድ በውል ከሚታወ የገበያ ቀንና ስፍራ ያላቸውንና ከ1000 በላይ የቁም እንስሳት በአንድ የግብይት ማስተናገድ የሚያስችል መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት በሁለተኛ ደረጃ የቁም እን ግብይት ማዕከልነት ይሰይማል፡፡

2. እነዚህን የግብይት ማዕከላት ለትራንስፖርት እና ለሌሎች መሰረተ ልማቶች በደንቡ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ታይተው የማያሟሉ ከሆነ በሂደት በሚመረጡ ቦታ እንደ አስፈላጊነቱ ሊለወጥ ይችላል፡፡

ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

3. በተጨማሪም የቁም እንስሳት ምርት ፍሰት በማጥናት ተጨማሪ የገበያ ማዕከላት እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡
4. በየደረጃው የሚገኝ አግባብ ያለው የክልል አካል የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትን ብዛትና ስርጭት ሲወስን ከግምት ማስገባት የሚኖርበት መስፈርቶች በዚህ መመሪያ ላይ ለመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ከተቀመጡት መስፈርቶች በተጨማሪ፤
   4.1. የታመሙ እንስሳት ማግለያ ያለው፣
   4.2. ለተጫራቾች መጠለያ ዳስ እና የጨረታ ማካሄጃ ስገነት፣
   4.3. የውሃ፣ የመብራትና የስልክ አገልግሎት፤ የጥበቃና ለገበያ ማዕከሉ ሰራኞች ቢሮ ያለው፡፡
   4.4. የእለታዊ የገበያ መረጃ ማሳወቂያ ቦርድ ሊኖራቸው ይገባል፤
   4.5. የተለያዩ የቁም እንስሳት ዓይነቶችን ለመመዘን የሚያስችሉ የተለያዩ ሚዛኖች ሊኖሩት ይገባል፤

## 8. የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት አስተዳደር

1. የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላትን የሚያስተዳድረው የከተሞች መስተዳድር ወይም የማዘጋጃ ቤቶች የሚመራው የግብይት ማዕከሉ በሚገኝበት ክልል የሚገኙ የግብርና ጽ/ቤት፤ የእንስሳት ኤጀንሲ ጽ/ቤት ከገቢዎችና ጉምሩክ እና እንደአስፈላጊነቱ ሌሎችንም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሚያካትት ኮሚቴ ያስተዳድራቸዋል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀጽ 3,4,5,6,7,8 የተጠቀሱት ለሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላትም ያገለግላል፡፡
3. የቁም እንስሳት ግብይት በግብይት ማዕከላት ውስጥ በድርድር ላይ ተመስርቶ ሲከናወን የዋጋ ውል ስምምነት የሚወሰነው በገዥና ሻጭ መካከል የወቅቱን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ይሆናል፡፡
4. የጨረታ የግብይት ስርዓትን ለመዘርጋት ጨረታ በቅድሚያ የሚካሄድባቸውን የገበያ ቦታዎች መለየትና ማደራጀት፣ ስርዓቱን በባለቤትነት የሚመራ አካል መሰየምና በየግብይት ማዕከላት አጫራቾችን አሰልጥኖ በአስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን በማደራጀት የማስማራት ወዘተ. በቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶአቸው የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሶስት

## 9. የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት የጨረታ አተገባበር ሂደት እና የግብይት ተዋንያኖች ግዴታዎች

1. የግብይት ሂደቱ የዋጋ አወሳሰን ግልፅና ቀልጣፋ ለማድረግ በጨረታ ላይ ተመስርቶ ሲሆን ዋጋዉም እንደ የቁም እንስሳቱ ዝርያ፣ ዕድሜና ይዘት በክብደት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡
2. ጨረታውን በተሟላ ሁኔታ ለማካሄድ እንዲረዳ የቁም እንስሳት ገበያ ቦታዎች ለዚሁ በሚመች መልኩ ይደረጃሉ፡፡



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

3. ግብይቱን የሚመራው የመንግስት አካል አጫራቾች ስልጥነው ይመደባሉ፤ የግብይት እንቅስቃሴውንም ይመራሉ፡፡ አስፈላጊውን መረጃም መዝግበው ይይዛሉ፡፡

4. የጨረታ ሂደቱን ለመምራት አመቺ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ይሟላሉ፤

ሀ/ የድምጽ ማጉሊያ መሳሪያ፣
ለ/ የእንስሳት ማመላከቻ ዘንግ፣
ሐ/ የአሸናፊ መለያ ምልክት፣
መ/ የእለታዊ መጫረቻዎች መሰብሰቢያና ማጠናቀሪያ ማህደር፣
ሠ/ ለጨረታ የሚቀርቡ እንስሳት መታያ ቦታ፣
ረ/ የተሸጡ እንስሳት መለያ ቦታ፣

5. የአጫራቾች ስልጣንና ተግባራት፣

ሀ. ገበያ በሚቆምባቸው ቀናት ሁሉ የመጫረቻ ቦታዎችን ለጫራታ በሚያመች መልኩ ያመቻቻል

ለ. የጨረታውን ሂደት የሚያስጀመረው የጨረታውን ፍትሃዊነት ለመከታተል የሚሰየሙ ታዛቢዎች ሲሟሉ ይሆናል፡፡

ሐ. አጫራቹ ለጨረታ የቀረቡትን የቁም እንስሳት በደረጃ አውጭዎች የቁም ክብደትንና ሌሎች የእይታ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የወጣላቸውን ደረጃ በፅሁፍ በመያዝ እንስሳቱን ወደ ተዘጋጀላቸው የማጫረቻ ስፍራ የመምራት፣

መ. እንስሳት ወደ መጫረቻው ስገነት እንዲገቡ በማድረግ ለማጫረት በተዘጋጀው ፎርም ላይ አስፈላጊውን መረጃ ይሞላል

ሠ. አጫራቹ ለጨረታ የቀረቡትን በነጣላ፣ በጥንድ ወይም በመንጋ የቀረቡትን እንስሳት ለማጫረቻ በተለየ የጨረታ ማሳያ ቦታ (ግርግም) ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል፣

ረ. ከእንስሳቱ ባለቤት የእንስሳውን የጨረታ የመነሻ ዋጋ በመቀበል ለተጫራቾች ጨረታውን ይመራል፣

ሰ. ወደ መጫረቻ የገቡትን እንስሳት በግልጽ ጨረታ ያጫርታል

ሸ. ከተለያዩ ተጫራቾች የሚሰጠውን ዋጋ ይመዘግባል ለተጫራቾች ያሳውቃል

ቀ. የአንድ እንስሳ የጨረታ መጨረሻ ለጨረታ በቀረበው እንስሳ ቀጣይ ተጫራች የጠፋ እንደሆነ የጨረታው ማብቂያ ይሆናል፣

በ. የመጨረሻውን እና የጨረታውን ዋጋ እንዲሁም የጨረታውን አሸናፊ ዝርዝር መረጃ ይይዛል የጨረታውን ዋጋ እና አሸናፊ ያሳውቃል፡፡

ተ. አጫራቹ የጨረታውን አሸናፊ በውል ሲያውቅ የቅድመ ግገርና የሽያጭ ውል መፈፀሚያ ስምምነት ያፈራርማል፤



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

ቸ. ለጨረታ ግብይት ቀርቦ በእለቱ ያልተሸጠ እንስሳ ከማጫረቻ ቦታው እንዲወጣ ያደርጋል፣

ኃ. አጫራቹ የጨረታ ሂደት በቁም ክብደት እንደጠበቀ ሆኖ በተናጠልና በመንጋ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፣

ነ. አጠቃላይ መረጃውን በዋና መዝገብ ላይ ይመዘግባል

ኘ. ማንኛውም የጨረታ ተሳታፊ ለጨረታ መነሻው 50 በመቶውን በባንክ ዝግ አካውንት እንዲያስቀምጥ ማስደረግ፤ ሽያጩ ሲጠናቀቅ የግዢውን ጠቅላላ ዋጋ ለሻጭ መክፈሉን ማረጋገጥና ጫረታውን የሚያፈርስ ከሆነ ግን ካስያዘው ገንዘብ 10 በመቶ ለገበያ ማዕከሉ በመቀጫነት ገቢ እንዲሆን ተደርጎ ቀሪው ለሻጭ እንዲከፍል ያደርጋል።

## 10. <u>የቁም እንስሳት የጨረታ ግብይት ተሳታፊዎች ግዴታዎች</u>

1. የገዢ ግዴታዎች

ሀ. እንስሳትን በጨረታ ከጨረታ ገበያ ማዕከላት መግዛት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቅድሚያ የገዢነት ቁጥር ከጨረታ የገበያ ማዕከል ውስጥ ማግኘት ይኖርበታል፣

ለ. የገዢ ቁጥር ለማግኘት ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ እና የንግድ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፣

ሐ. በአንድ የጨረታ ቀን የተሰጠ ቁጥር የሚያገለግለው ለአንድ ቀን ብቻ ስለሆነ በዕለቱ መጠቀም አለበት፣

መ. ገዢ የጨረታውን ውጤት በውል ሲያውቅ የቅድመ ግዢና የሽያጭ ውል መፈፀሚያ ስምምነት የመፈረም/ ክፍያ የመፈፀም፣

ሠ. የጨረታው አሸናፊ ያሸነፈበትን የጨረታ ዋጋ 50 በመቶ በዝግ አካውንት በመክፈል ለእንስሳቱ የግል መለያ ያሰጣል፣

ረ. አስፈላጊውን የዝውውር ፈቃድ፣የጤና ሰርተፍኬት እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ከሻጭ ወይም ከገበያ ማዕከሉ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ተቆጣጣሪ አካል የመረከብ፣

ሰ. ለጨረታ ግብይት የጨረታ ማዕከል ውስጥ የገባውን እንስሳ ለመግዛት የተጫረተ ማንኛውም አካል የተጫረተበትን እንስሳ በአፋጣኝ ያሸነፈበትን ሙሉ ዋጋ የመክፈል፣

ሸ. ማንኛውም የጨረታ ተሳታፊ ከጨረታ መነሻው 50 በመቶውን በባንክ ዝግ አካውንት በማስያዝ ጨረታውን ይሳተፋል፣

ቀ. የጨረታውን 50 በመቶ በማስያዝ በጨረታው የተሳተፈ ተጫራች የጨረታውን ስርዓት የሚያፈርስ ከሆነ በዝግ አካውንት ካስያዘው ገንዘብ 10 በመቶ ለገበያ ማዕከሉ በመቀጫነት ገቢ እንዲያዲሆን ተደርጎ ቀሪው ለሻጭ ይከፈላል።



ክቡር ጫኔ
ሚኒስትር

የሻጭ ግዴታዎች

ሀ. ማንኛውም ሻጭ ለጨረታ ያቀረባቸውን የቁም እንስሳት በደረጃ አውጭዎች የቁም ክብደትንና ሌሎች የእይታ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የወጣላቸውን ደረጃ በፅሁፍ በመያዝ እንስሳቱን ወደ ተዘጋጀላቸው የማጫረቻ ስፍራ የማምጣት፣

ለ. እንስሳት ወደ ማጫረቻው ሰገነት እንዲገቡ በማድረግ ለማጫረት በተዘጋጀው ፎርም ላይ አስፈላጊውን መረጃ ይሞላል፡፡

ሐ. የጨረታ የመነሻ ዋጋ ለአጫራቹ በመስጠት ጨረታውን ይከታተላል፣

መ. የመጨረሻውን የጨረታ ዋጋ እንዲሁም የጨረታውን አሸናፊ ዝርዝር መረጃ ከአጫራቹ ይረከባል፡፡

ሠ. ከአጫራቹ የጨረታውን የማሸነፊያ ዋጋ እና የአሸናፊውን ግለሰብ በውል ሲያውቅ የቅድመ ግዢና የሽያጭ ውል መፈፀሚያ ስምምነት ይፈራርማል፤

ረ. ለጨረታ ግብይት ቀርቦ በእለቱ ያልተሸጠ እንስሳ ከማጫረቻ በረቱ እንዲወጣ ያደርጋል፣

ሰ. ከጨረታው አሸናፊ የጨረታ ዋጋ በመቀበል ለእንስሳቱ ገዢ አስፈላጊውን የጤና ሰርተፍኬት እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎች ያስረክባል፣

## ክፍል አራት

## 11. ስለ ቁም እንስሳት ህገወጥ ንግድ ቁጥጥር አሠራር፣

1. የቁም እንስሳት አጓጓዥ የቁም እንስሳትን ከግብይት ማዕከላት፤ ከማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያዎች፤ እንዲሁም ከኳራንታይን ጣቢያዎች ወዘተ ወደ ቀጣይ መዳረሻ ቦታዎች ከመጓጓዙ በፊት አግባብ ባለው አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የማጓጓዣ ፈቃድ ማግኘቱንና መያዙን ማረጋገጥ፡፡
2. የቁም እንስሳት ግብይት ቁጥጥር በፌዴራልና በክልል ደረጃ በሚሰየሙ የቁም እንስሳት ግብይት ተቆጣጣሪዎች አማካይነት የሚከናወን ሲሆን ክልሎች የቁም እንስሳት መቆጣጠሪያና ምዝገባ ጣቢያዎችን በወረዳ ደረጃ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነታቸው በታመነባቸው ቦታዎች ላይ ተጨማሪ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን ያቋቁማሉ፡፡
3. ክልሎች እንደ አስፈላጊነቱ ተቆጣጣሪዎችን በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ሊመድቡ ይችላሉ፡፡
4. በፌዴራል ደረጃም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሕገወጥ የቁም እንስሳት እንቅስቃሴን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ጣቢያዎች በከተሞች መግቢያና መውጫ ላይ እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

## 12. በሃገር ውስጥ ህግን በመተላለፍ ስለተያዘ የቁም እንስሳት

1. የተያዙ እንስሳትን በተመለከተ ንግድን የሚያስተዳድሩ አካላት የህግ አፈጻጸሙን ሙሉ ሀላፊነት ወስዶ ይከታተላል አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል።
2. ከተያዙት እንስሳት ውስጥ በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚከሰቱ የእንስሳት ድንገተኛ ሞት ሲያጋጥም ያገዥ ክፍል፣

   ሀ/ በአቅራቢያው ካለው የእንስሳት ጤና ጥበቃ ክፍል የእንስሳውን ሞት ምክንያት የሚያረጋግጥ ህጋዊ የምስክር ወረቀት፣

   ለ/ ይህንንም የሞት የምስክር ወረቀት በመያዝ በአቅራቢያ ለሚገኘው የፀጥታ አካል ማሳወቅ ፣

   ሐ/ የቁም እንስሳትን ድንገተኛ ሞት በተመለከተ የሞተውን እንስሳ በድን በአግባቡ ማስወገድ አለበት፣

   መ/ ያዢው ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን መረጃዎች በተጠናቀረ መልኩ ካቀረበ ቀደም ሲል ተረክቦ ለጎደሉት እንስሳት ተጠያቂ አይሆንም።

   ሠ) የቁም እንስሳቱ ሽያጭ ገንዘብ በፍትህ አካል ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ገንዘቡ በዝግ የባንክ ሂሳብ አደራ ይቀመጣል።

   ረ/ የተያዙት የቁም እንስሳት በሚመለከተው የመንግስት አካል ህገወጥ አለመሆኑ ከተረጋገጠ በማንኛውም በሰነድ የተደገፈ ወጪዎች ተቀናንሰው በዝግ የባንክ ሂሳብ አደራ የተቀመጠው ገንዘብ የቁም እንስሳው ለተወረሰበት ሰው ይመለሳል።

   ሰ/ በህገ ወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የተያዙ የቁም እንስሳትን ከተያዙበት ቀን ጀምሮ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ለሚቆዩባቸው ቀናት የሚያስፈልግ ልዩ ልዩ ወጪዎችን በተያዙበት አካባቢ የሚገኘው አግባብ ያለው አካል የሚሸፈን ሆኖ ውሳኔ ካገኙ በኋላ ከሽያጭ ገንዘቡ ተከፋይ ይሆናል።
3. ለተያዙት እንስሳት የህግ ውሳኔ እስኪያገኙ ድረስ በአካባቢው የሚገኘው መስተዳድር የማቆያ ቦታ በቅድሚያ ማመቻቸት ይኖርበታል።

## 13. የቁም እንስሳት ዝውውርና አጓጓዝ ስርዓት

### የቁም እንስሳት ዝውውር ስርዓት

1. በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ እንዲሁም በክልል ዋና ከተሞች፤ በዞን ዋና ከተሞች እና በሌሎች የሪፎርም ከተሞች ማንኛውም የቁም እንስሳት የጋማ ከብቶችን ጨምሮ በአስፋልት መንገዶች ላይ በእግር መንዳት የተከለከለ ነው፣ ሆኖም አርቢዎች ለህክምና ለግጦሽ እና ወደ ግብይት ማዕከላት ሲያዘዋውሩ ሸማቾች ወደ እርድ ቦታዎችና መኖሪያ ቤታቸው ማዘዋወር አይከለከልም፤

2. በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የጋማ ከብቶች ለበዓላት፣ ለሃይማኖታዊ ስርዓቶች እና መሠል ክንዋኔዎች ብቻ በተመረጡ መንገዶች ማዘዋወር ይቻላል፣



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

3. የቁም እንስሳትን ለግጦሽ ከሚያንጉዙ አርቢዎችና ለግል ፍጆታ ከአቅራቢያቸው ግብይት ማዕከል ገዝተው ከሚያንጉዙ ሸማቾች በስተቀር ማንኛውም ሰው የቁም እንስሳትን ከቦታ ቦታ የሚያንጉዝ አካል በማጓጓዝ ሂደት የማጓጓዣ ፍቃድ የምስክር ወረቀት መያዝና እና አግባብ ባለው አካል ሲጠየቁም ማሳየት አለባቸው፡፡

4. የቁም እንስሳትን ከመጀመሪያ እና ከሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት በመግዛት እያጓዘ ያለ የግብይት ተዋናይ የቁም እንስሳቱን በማጓጓዣ ፍቃድ የምስክር ወረቀቱ ላይ የተገለጸው የቁም እንስሳት አይነትና መጠን ብቻ መሆኑ፣ በወቅቱና በአግባቡ ወደ ተጠቀሰው ስፍራ ስለማድረሱ አግባብነት ያለው አካል ወይም የግብይት ተቆጣጣሪዎች ሊያጣሩ ይችላሉ፡፡

5. በግብይት እንቅስቃሴ ወቅት የቁም እንስሳት ከ50 ኪ.ሜ በላይ በእግር መጓጓዝ ስለሌለባቸው የጉዞ መሸኛ የሚሰጠው በእግር ለማጓጓዝ ለሚፈልጉ የጉዞ መሸኛ ከሚሰጥበት ቦታ እስከ መዳረሻ ቦታው ድረስ ያለው ርቀት ከ50 ኪ.ሜ በታች መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

6. የጉዞ መሸኛ ከሚሰጥበት ቦታ እስከ መዳረሻ ድረስ ያለው ርቀት ከ50 ኪ.ሜ በላይ ከሆነ በእግር መጓጓዝ ስለሌለባቸው የጉዞ መሸኛው በመኪና ተብሎ እንጂ በእግር ተብሎ መሰጠት የለበትም፡፡

7. የቁም እንስሳትን አጓጓዥ የቁም እንስሳቱ ህጋዊ ስለመሆናቸው እና የእንስሳት ዝውውር ፈቃድ እንዲሁም ግዢ የተፈፀመበትን ደረሰኝ በአጠቃላይ የተሟላ መረጃ መያዙን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

8. የቁም እንስሳት ደረጃውን በጠበቀ የቁም እንስሳት ማጓጓዣ መጓጓዝ ይኖርባቸዋል፡፡ የቁም እንስሳትን ማጓጓዝ ዝርዝርን በተመለከተ በመንገድ ትራንስፖርት መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

9. በግብይት እንቅስቃሴ ወቅት በተወሰኑ ህጋዊ ሰነዶች ጉድለት ሲገኝ እና የቁም እንስሳቱ በኬላ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎቹ ሲያዝ፣

ሀ/ የቁም እንስሳቱ በአግባቡ ተራግፈው ወደ ጊዜያዊ ማረፊያ በረት እንዲገቡ ይደረጋል፣

ለ/ ሁኔታው በአስቸኳይ ተጣርቶ ህገወጥ አለመሆናቸው ከተረጋገጠ እና አስፈላጊው የማስተካከያ ወይም የእርምት እርምጃ ከተወሰደ እና ህጋዊ ሂደቱን የተከተለ ስለመሆኑ በግብይት ተቆጣጣሪው አካል ከተረጋገጠ በኋላ የማጓጓዣ ፍቃድ የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት ወደ ቀጣይ መዳረሻ ስፍራ እንዲጓዙ ይደረጋል፣



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

## ክፍል አምስት

## የቁም እንስሳት የግብይት ተዋናያኖች እና ከግብይቱ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ስለአላቸው አካላት ግዴታ

### 14. የቁም እንስሳት የግብይት ተዋንያኖች ግዴታ

1. በግብይት ማዕከላት ውስጥ የቁም እንስሳትን ለመሸጥ የንግድ ፈቃድ ወይም ተወካይ ከሆነ የውክልና ማስረጃ የመያዝና በግብይት በተቆጣጣሪ ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፤
2. በግብይት ማዕከላት ውስጥ የሚሰጡትን አገልግሎቶች እና አገልግሎት መስጫዎች ከግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ዕውቅና እና ስምምነት ውጪ መያዝና መጠቀም የለበትም፤
3. በግብይት ማዕከላት ውስጥ የግብት ተዋናይ አገልግሎት የሚያገኘው በግብይት ማዕከላት ተቆጣጣሪው ወይም የግብይት ማዕከሉን ከሚያስተዳድረው አካል እውቅና በተሰጠው ሰው ብቻ ነው፡ ለሚያገኘውም አገልግሎትም ክፍያ በታሪፉ መሰረት መፈጸም አለበት።
4. አንድ የቁም እንስሳን በእዚያው ገበያ ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ ግብይት አይካሄድበትም።
5. ከአርቢው በስተቀር ማንኛውም የቁም እንስሳት ሻጭ ለሚሸጠው የቁም እንስሳ ለገዢዎች ደረሰኝ መስጠት አለበት።
6. የገበያውን ሰላማዊ ግብይት የሚያደፈርሱትን ወይም እንቅፋት የሚሆኑትን ችግሮች ከግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ወይም የግብይት ማዕከሉን ከሚያስተዳድረው አካል ጋር በጋራ በመሆን መፍታት አለበት።
7. ከግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ወይም የግብይት ማዕከሉን ከሚያስተዳድረው አካል የሚጠየቁ መረጃዎችን መስጠት አለበት።
8. ለሽያጭ ያቀረበው እንስሳ በበሽታ ወይም በሌላ ምክንያት ቢሞትበት ከግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ጋር በመተባበር በድኑ እንዲነሳ የማድረግ ግዴታ አለበት፤
9. የገበያውን ንፅህና የመጠበቅ ድርሻውን መወጣት ኃላፊነት አለበት።
10. ማንኛውም የቁም እንስሳ ገዢ የገዛበትን ደረሰኝ እና የማንነት መለያ መታወቂያውን በግብይት ማዕከሉ ውስጥ በተቆጣጣሪዎች ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፤
11. ማንኛውም የቁም እንስሳት ገዢ የገዛውን የቁም እንስሳ ከገበያው በዕለቱ ማስወጣት አለበት።
12. ማንኛውም የቁም እንስሳት ተዋንያን የጉዞ መሸኛ ሲጠይቅ ትክክለኛ መዳረሻ ቦታውን የሚገልጽ ማስረጃ የማሳየት እና ወደ ትክክለኛ መዳረሻ ቦታው ብቻ የመጠየቅ እና የመቀበል እንዲሁም የማጓጓዝ ግዴታ አለበት።
13. የቁም እንስሳትን ወደ ግብይት ማዕከላት ለሽያጭ ሲቀርቡ ያለአግባብ እና ሆንተብሎ ለማሳሳት ክብደት እንዲጨምሩ ለማድረግ ከሚደረጉ ነገሮች ከማድረግ የመቆጠብ፤ የቁም እንስሳት ማድለቢያ ወይም ማቆያ ጣቢያውን አግባብ ያለው አካል በአካል በመገኘት ለመጎብኘት ሲፈልግ የመተባበር ግዴታ አለበት፤



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

14. ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ በተሠማራበት የሥራ መስክ በሰጠው አገልግሎት የግብይት ማዕከሉን የሚያስተዳድረው አካል በወሰነለት ታሪፍ መሠረት ተገቢውን ክፍያ ሲጠይቀው የመክፈል ግዴታ አለበት፤

## 15. የአርቢ ግዴታዎች

ማንኛውም በቁም እንስሳት ግብይት ላይ የተሰማራ አርቢ፣

1. ማንኛውም አርቢ ከመኖሪያ ቦታው ርቀ የቁም እንስሳትን ወደ ሁለተኛ ደረጃ የግብይት ማዕከላት ይዞ ሲመጣ ከአካባቢው መስተዳዳር አካላት በዘመኑ የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ይዞ መገኘት አለበት።
2. ማንኛውም አርቢ የቁም እንስሳትን በቀጥታ ወደ ውጪ ለመላክ ከፈለገ እንደማንኛውም የቁም እንስሳት ላኪ የላኪነት የንግድ ፍቃድ ማውጣት አለበት።

## 16. የባለቄራዎች ግዴታዎች

ማንኛውም ባለቄራ፣

1. ህገ ወጥ ግብይት የተፈፀመባቸውን የቁም እንስሳት እርድ ያለመፈጸም፤
2. ወደ ቄራው ለዕርድ አገልግሎት የሚመጡትን የቁም እንስሳት ሙሉ መረጃ የመጠየቅ፤
3. ለግል ፍጆታቸው ለመጠቀም የቁም እንስሳትን ከግብይት ማዕከላት ገዝተው ወደ ቄራ በትክክል ለማስገባታቸውና በቄራው ለማሳረዳቸው ማስረጃ የመስጠት፤

ግዴታዎች አሉበት።

## 17. የባለልኳንዳ ቤቶች ግዴታዎች

ማንኛውም ባለልኳንዳ ቤት፣

ህገ ወጥ ግብይት የተፈፀመባቸውን የቁም እንስሳት ለዕርድ አለማዋል፤

ግዴታዎች አሉበት።

## 18. የቁም እንስሳት አጓጓዦች ግዴታ

1. የቁም እንስሳትን ለመጫን የተዘጋጀው ተሽከርካሪ የቁም እንስሳቱን ጤንነትና ጥራት ሊያጎድሉ ከሚችሉ ከማናቸውም ባዕድ ነገሮች የጸዳ መሆኑን የማረጋገጥ፤
2. የቁም እንስሳቱ ህጋዊ ስለመሆኑ በተቆጣጣሪው የተሰጠውን መሸኛ ወረቀት የመያዝና አግባብ ባለው አካል በተመደበ ተቆጣጣሪ ሲጠየቅ የማሳየት፤

የኢፌዲሪ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሚኒስቴር

ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

## 19. በቁም እንስሳት የግብይት ማዕከላት ውስጥ የአገልግሎት ሰጪ ግለሰቦች ወይም በማህበር የተደራጁ አካላት ግዴታዎች፤

1. ማንኛውም አገልግሎት ሰጪ ግለሰብ ወይም በማህበር የተደራጀ አካል የገበያ ማዕከሉን ከሚያስተዳድረው አካል ፈቃድ ሳያገኝ በቁም እንስሳት ገበያ ውስጥ መግባትም ሆነ አገልግሎት ያለመስጠት፤
2. አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ በመያዝ እንደ አስፈላጊነቱ በግብይት ማዕከሉ ተቆጣጣሪ ሲጠየቅ የማሳየት፤
3. በገበያ ማዕከሉ ውስጥ እንዲሰራ ከተፈቀደለት የሥራ መስክ ውጪ ሌላ ስራ ላይ ያለመስራት፡፡
4. ለሰጠው አገልግሎት ከታሪፍ ውጪ ጭማሪ ክፍያ ያለመጠየቅ እና ያለመቀበል፣
5. ለሰጠው አገልግሎት ክፍያ ደረሰኝ የመስጠት፡፡
6. ቀደም ብሎ የሥራ መለያ ልብስ እና የደረት መታወቂያ ባጅ ለቢሮው በማሳወቅ ዘወትር በሥራ ሰዓት የመልበስና የማድረግ፡፡
7. በገበያው ውስጥ የሚከሰቱ ህገ ወጥ የሆኑ ተግባራትን ለቢሮው የማሳወቅና የመከላከል፡
8. የአገልግሎት ሰጪው አካል በማህበር የተደራጀ ከሆነ የማህበሩ አባል በገበያው ውስጥ ህገ-ወጥ ስራ ሲሰራ የግብይት ማዕከሉ ወይም በተቆጣጣሪዎች ከተደረሰበት ማህበሩ የወሰደውን የቅጣት እርምጃ ለግብይት ማዕከሉ በጹሁፍ የመግለጽ
ግዴታ አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 20. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በማክበር፤ በማስከበርና በማስፈጸም ረገድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## 21. በሚ/ር መ/ቤቱና በክልል አካላት መካከል ስለሚኖር ግንኙነት

1. አግባብነት ያላቸው የክልል ቢሮዎች በክልላቸው ከሚገኙት ዞኖች፤ ከተማ መስተዳድሮችና ወረዳዎች አጠቃላይ የቁም እንስሳት ግብይት መረጃዎችን ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በየወሩ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በተጠየቀ ጊዜ መረጃ ያስተላልፋሉ፤
2. ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አግባብነት ካላቸው ከክልል ቢሮዎች በክልላቸው ከሚገኙት ዞኖች፤ ከተማ መስተዳድሮችና ወረዳዎች የተሰበሰበውን የቁም እንስሳት ግብይት መረጃዎች ተንትኖ ውጤቱን በግብረ መልስ መልክ ለክልል ቢሮዎች ያስተላልፋሉ፤



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

3. በቁም እንስሳት ንግድ ስራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ላይ መወያየት የሚያስችል የጋራ መድረክና ሌሎች የአሰራር ሁኔታዎች ዕቅድ ሪፖርት፣ አውደ ጥናት፣ ስልጠናና የመሳሰሉት በሚኒስቴሩና በክልል ቢሮዎች በጋራ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባቸዋል፡፡

## 22. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ የካቲት 30, 2007 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ከበደ ጫኔ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ የንግድ ሚኒስትር



ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

**<u>በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ</u>**

**<u>ንግድ ሚኒስቴር</u>**

ሴሪ ቁጥር No:------------------

ቀን ---------------

## <u>የቁም እንስሳት ለሚያዝባቸው ግለሰቦች የሚሰጥ ደረሰኝ</u>

በ ------------------------ ፍተሻ በር በ ------------------------------ ከተማ ------------------------------

ቀበሌ ---------------------- ከፍተኛ ---------------------- የቤት ቁጥር ----------------------- ኗሪ ከሆኑት

ከ ------------------------ መታወቂያ ቁጥር ----------------------- ለ ------------------------------------ክልል

ንግድ / ግብይትና ኅ/ ሥራ ቢሮ ወይም ንግድ ሚኒስቴር የማስረክበው -----------------------------------

የቁም እንስሳት ተቀብያለሁ።

የቁም እንስሳውን የተረከበው የኬላ ተቆጣጣሪ ስም ---------------------------------

የመታወቂያ ቁጥር -------------------------------

የኬላ ተቆጣጣሪ ፊርማ ---------------------------

የቁም እንስሳቱ የተወረሰበት ግለሰብ ስም -------------------

ፊርማ ------------------

<u>ማሳሰቢያ፡-</u>

1. ይህ ደረሰኝ የቁም እንስሳ በመጠቆም ፣በማስያዝ እና በማስረከብ ሚኒስቴሩን ለሚረዱና አበል ለሚያገኙ የሚሰጥ ስላልሆነ ይህን አገልግሎት የሚሰጡ ግለሰቦች ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ሌላ ደረሰኝ መውሰድ ይኖርባቸዋል።
2. ይህ ደረሰኝ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ የመጀመሪያው (ዋናው ነጩ) የቁም እንስሳቱ ለተያዘበት ግለሰብ ወይም የመኪናው ሰሌዳ ጎን ቁጥር እየተጻፈበት ለመኪናው ሾፌር ፣ሁለተኛው (ሮዝ ) የቁም እንስሳቱን ለክልል ንግድ /ግብይትና ኅ/ሥራ ቢሮ ወይም ለንግድ ሚኒስቴር በሚያስረክቡበት ጊዜ ከቁም እንስሳቱ እና ከዝርዝር መግለጫ ጋር ለክልል ንግድ /ግብይትና ኅ/ሥራ ቢሮ ወይም ለንግድ ሚኒስቴር ተረካቢ ይሰጥ እና ሶስተኛው ኮፒ (ሰማያዊው)በጥራዙ ላይ እንዳለ ለቁጥጥር ይቀመጣል።

ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድ ሚኒስቴር**

**በቁም እንስሳትና ቆዳና ሌጦ ግብይት ዳይሬክቶሬት**

**የቁም እንስሳት የጉዞ መሸኛ ፍቃድ**

ሴሪ ቁጥር ---------- No ----------

1. የቁም እንስሳቱ ባለንብረት/ድርጅት፣ ስም፣ ------------------- የንግድ ፍቃድ ቁጥር --------------የታደሰበት---------------- ዓም ----------- ክልል --------- ዞን ---------- ወረዳ --------- ከተማ ------------ ቀበሌ -----------የቤት ቁጥር ---------- ስልክ ቁጥር /ሞባይል/---------- ስልክ ቁጥር የቢሮ/የቤት --------------------------

2. የቁም እንስሳቱ ዓይነትና ብዛት፤- 2.1. የዳልጋ ከብት ብዛት--------------,

   2.2. የበግ ብዛት፤---------------- ,

   2.3. የፍየል ብዛት፤--------------,

   2.4. የግመል ብዛት፤---------,

   2.5. ሌላ ብዛት፤--------------

3. የቁም እንስሳቱ የመለያ ቁጥር፤- ----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------
----------------------------------------------------------------------------------------------------

4. የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር ዋና ------------------ ተሳቢ --------------- የጎን ቁጥር ---------------------------

5. የአሽከርካሪው፡- መንጃ ፍቃድ ቁጥር ----------------------- ክልል --------------- ዞን --------------ወረዳ ----------

   ከተማ ----------- ቀበሌ --------------- የቤት ቁጥር -------------- ስልክ ቁጥር/ሞባይል/-----------------

6. የቁም እንስሳቱ የተሸኘበት ጣቢያ /የጉዞ መነሻ ቦታ/ ክልል -------------- ዞን ---------------ወረዳ ----------

   ልዩ ቦታ -------------------- የተሸኘበት ቀን -------------------- ሰዓት ------------------

7. የመድረሻ ቦታ ፤- ክልል --------------- ዞን ------------------- ወረዳ ---------------------- ልዩ ቦታ -----------------

   የመድረሻ ቀን ------------------ ሰዓት ----------------

8. የቁም እንስሳቱ ባለንብረት ሙሉ ስም፤ ------------------------ ፊርማ --------------- ቀን ---------------

9. የአሽከርካሪው ስም --------------------------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን ---------------

10. የሸኘው ሰራተኛ ስም --------------------------------------------- ፊርማ ------------------ ቀን ---------------

<u>ማሳሰቢያ</u> ፦

1. ይህ ቅጽ ስርዝ ድልዝ ካለው ተቀባይነት አይኖረውም፤
2. ማንኛውም የቁም እንስሳትን ጭኖ የሚያጓጉዝ አሽከርካሪ ይህን መሸኛ ወረቀት መያዝና በመንገድ ላይ በህጋዊ አካል ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፤
3. ይህ ቅጽ በአራት ኮፒ ተሰርቶ ዋናው ለአሽከርካሪው፤ ሁለተኛው ኮፒ ለእንስሳቱ ባለንብረት፤ ሶስተኛው ኮፒ ለቁም እንስሳት ግብይት ዳይሬክቶሬት፤ አራተኛው ኮፒ ከፋይል ጋር ይያያዝ፤
4. ይህ መሸኛ ከ -------------------- ቀን በኋላ አይሰራም፡

ከበደ ጫኔ
ሚኒስትር